# ክብር ለኢትዮጵያ ክብር ለብርቱኳን

## አንደኛ ዓመቱን ያስቆጠረው የብርቱኳን ሚዴክሳን መታሰር ምክንያት በማድረግ በሰሜን አሜሪካ በዋይት ሀውስ ፊት ለፊት በተደረገው የሻማ መብራት ስነስርዓት

የኛ መመኪያ ተስፋ ለብዙሃን
እህት እናታችን እምዬ - ብርሃን
ፍትሕ አማላጅዋ የወገን መድህን
ክብር ላንቺ ይሁን! ለታጋይዋ ብርቱኳን።

ለሰው ልጅ ነፃነት ለመልካም አላማ
እንደ ማንዴላ እንደ ባራክ ኦባማ
መፈክር አንግባ የለውጥ አርማ
ትግል አቀጣጠለች በፅናት ቆማ።

ፈር ቀዳጅ አዲስ ጎዳና
ትውልድ ለማዳን ከጭቆና
ከረሃብ ከስደት ከልመና
ከጦርነት ግድያ ከአፈና
ለሰላም ለዕድገት ለብልፅግና
ቆርጣ ስትታገል ምሳሌ ሆና!

ተረባረቡባት ባንዳ ለባንዳ
በሰደፍ ጠመንጃ እየነዳ
ታሰረች ወህኒ ቤት ወርዳ
የቂም በቀል የህዝባችን ፍዳ
ከፋይ ሆነች የሁላችን ዕዳ።

ተቆልፎ እግር ብረት
እንደ ውሻ በሰንሰለት
በጨለማ ጠባብ ቤት
ጋሃነም ኑሮ ብቸኝነት
ዓለም በቃ እስከ ህልፈት
ጊዜው ተቆጠረ እኖሆ አንድ ዓመት።

የኛ መመኪያ ተስፋ ለብዙሃን
እህት እናታችን እመ - ብርሃን
ፍትሕ አማላጅዋ የወገን መድህን
ክብር ላንቺ ይሁን! ለታጋይዋ ብርቱኳን።

የጠላት ጭካኔ ምንም ሳትፈራ
ለነፃነት ዋጋ ስትከፍል መከራ
መንፈስ ቃል ሆኖ ከወህኒ ቤት ሲጣራ
እኛስ ምን እንበል ምን እንስራ?

አዎ!!
ላንቺ ክብር ሻማ ላብራ
ባንቺ ጀግንነት እኔም ልኩራ
ባንቺ ፅናት ትግሉ ይጥራ
እንክርዳዱ ከምርቱ ይለይ ጎራ።

ብርቱኳን!!
ቃልሽ ሃያል ነው አለው ሚስጢር
ቃልሽ ሰላም ነው የሚያበስር
ቃልሽ ብርታት ነው የሚያጠነክር
ቃልሽ ተስፋ ነው የነገው ምስክር
ቃልሽ ፍቅር ነው ሁሉም የሚያስተባብር።

የኛ መመኪያ ተስፋ ለብዙሃን
እህት እናታችን እመ - ብርሃን
ፍትሕ አማላጅዋ የወገን መድህን
ክብር ላንቺ ይሁን! ለታጋይዋ ብርቱኳን።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!

ከገሠሠ እንግዳ
ህዳር 2009 ዋሽንግተን ዲሲ